የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ገንዘብ ቢሮ

በአማራ ክልል ውስጥ በተለያየ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ለመገመትና ደረጃቸውን ለመወሰን የወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር

152/2018

ነሐሴ 2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

መመሪያ ቁጥር 152/2018

በአማራ ክልል ውስጥ በተለያየ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ለመገመትና ደረጃቸውን ለመወሰን የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

በክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 3 መሠረት የደረጃ "ሐ"፣ "ለ" እና "ሀ" ግብር ከፋዮችን ደረጃ መወሰን የሚያስችለውን ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ መጠን በጥናት ላይ በመመስረት ቢያንስ በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ መሻሻል እንዳለበት በመደንገጉ፣

በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 48 ላይ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ገቢ ለመወሰን የቁርጥ ግብር አወሳሰን ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል የተቀመጠ ቢሆንም ጥናቱ በክልሉ ከተካሄደ ከአምስት ዓመት በላይ ያለፈው በመሆኑ አሁን ላይ ያለውን ሀገራዊና ክልላዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በትክክል በሚያሳይ መንገድ የግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ጥናት እንደገና በማጥናት የተሻለ ገቢ ለመሰብሰብ እና የደረጃ ምደባ ማካሄድ በማስፈለጉ፤

የመደበኛ ቁርጥ ግብር ጥናቱ በዋናነት የንግድ ሥራቸው ግለሰብ የሆኑ የደረጃ "ሐ" ፣"ለ" እና "ሀ" እና የኪራይ ገቢ ግብር ከፋዮች እንዲሁም የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው የንግድ ድርጅቶች ቀጥረው የሚያሰሯቸውን ሠራተኞች የሥራ ግብር መረጃ ማደራጀት በማስፈለጉ፤

በክልሉ ውስጥ በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ የተሠማሩ ወደ ግብር መረቡ ያልተካተቱ ግብር ከፋዮችን ለይቶ ሙሉ በሙሉ ወደ ግብር መረቡ በማካተት የሚፈለግባቸውን ግብር እና ታክስ በወቅቱ እንዲከፍሉ ለማድረግ በማስፈለጉ፤

የገንዘብ ቢሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በአማራ ክልል ውስጥ በተለያየ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ለመገመትና ደረጃቸውን ለመወሰን የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 152/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ የተሰጠው፡-

1/ "የግብር ከፋዮችን ደረጃ መወሰን" ማለት በቀን ገቢ ጥናት በሚገኘው መረጃ መሠረት የአንድ ግብር ከፋይ ወይም ድርጅት ዓመታዊ የንግድ እንቅስቃሴ ሽያጭ ላይ በመመሥረት ደረጃ "ሐ"፣ "ለ" እና "ሀ" ብሎ መወሰን ነው፣

2/ "ገቢ" ማለት መደበኛ ያልሆነ ገቢን ጨምሮ ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ወይም በማንኛውም መንገድ ለግብር ከፋዩ የተከፈለው፣ በስሙ የተያዘለት ወይም የተቀበለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ነው።

3/ "የቀን ገቢ" ማለት ግብር ከፋዩ በአማካይ በአንድ ቀን ውስጥ የሚያገኘው አጠቃላይ የዕቃ/የአገልግት ሽያጭ በብር ማለት ነው።

4/ "የጥናት ኮሚቴ" ማለት ጥናቱን ከታለመለት ግብ ለማድረስ የሚቋቋሙ እና የሚሰሩ የተለያዩ የኮሚቴ አባላትን ያካተተ የኮሚቴ ስብጥር ነው።

5/ "የቀን ገቢ ግምት ጥናት" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለሰብ ነጋዴዎችን ወይም ድርጅቶችን የንግድ እንቅስቃሴ በማጥናት ዓመታዊ የሽያጭ ገቢያቸውን ለመገመት የሚደረግ የመረጃ መሰብሰብ፣ የማደራጀት፣ የማጠናከር፣ የመተንተን እና የመገመት ሥራ የሚያጠቃልል ተግባር ነው።

6/ "የንግድ ሥራ ገቢ" ማለት በማናቸውም ሰው አማካኝነት ለትርፍ የሚከናወን የኢንዱስትሪ ፣ የንግድ ፣ የግብርና ፣ የሙያ ወይም የጣልቃ ገብ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም ፣ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንደ ንግድ ሥራ ዕውቅና ከተሰጠው ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ ሲሆን በገቢ ግብር አዋጅ 240/2008 በአንቀጽ 21 የተሰጠውን ትርጉም ይጨምራል።

7/ "ግብር ከፋይ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ወይም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ወይም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 283/2014 ዓ.ም ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 (የተሻሻለው) ወይም የከተሞች የገቢ አርዕስትና ታሪፍ መወሰኛ ደንብ ቁጥር 135/2008 ወይም በሌሎች በክልሉ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች የግብር ግዴታ ያለበት ወይም የተጣለበት ሰው ነው።

8/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብ ቢሮ ነው።

9/ "ገቢዎች ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢዎች ቢሮ እና እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን የተቋቋመ የገቢ ተቋም ነው።

3. <u>የጥናቱ መርህ</u>

1/ የታክስ ፍትሃዊነትን በግብር ከፋዮች መካከል /Vertical & Horizontal Equity/ ማስፈን፤

2/ የታክስ ተገማችነትን ለግብር ከፋዩና ለታክስ ሰብሳቢ ማረጋገጥ፤

3/ ከክልላዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የሚጣጣም የልማት ፋይናንስ ማመንጨት፤

4/ የንግድ እና የታክስ ህጎችን የበላይነት ማረጋገጥ፤

5/ ግብር ከፋዮች በቀን ገቢ ግምት ጥናት ዙሪያ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረጋገጥ፤

6/ የታክስ መሠረት ማስፋት፤

4. <u>የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን</u>

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደር ሥር ባሉ በግብር ከፋይነት በሚታወቁ የደረጃ "ሐ"፣ የደረጃ "ለ" እና የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች እና እስካሁን በግብር ከፋይነት ያልተመዘገቡትን ወይም በግብር መረቡ ያልተካተቱትን በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ ነጋዴዎች፣ ቤት/ህንፃ የሚያከራዩ ግለሰቦች፣ ማህበራት፣ አክሲዮንና የሽርክና ማህበራት፣ የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ድርጅቶች የሥራ ግብር ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጅቶች እና የንግድ ዘርፎች የቁርጥ ግብር ጥናቱ አያካትትም፡-

ሀ) በክልሉ ውስጥ ያሉ የሕግ-ሰውነት መብት /Legal entity/ ያላቸው ድርጅቶች ከኪራይና ሥራ ግብር ውጭ ያለውን ፤

ለ) በቁርጥ ግብር የተካተቱትን ጥብቅና፣ ወፍጮ ቤት እና የተሽከርካሪ አገልግሎት ንግድ ዘርፍ የተሠማሩትን፤

ሐ) በክልሉ ውስጥ ያሉ የሕግ-ሰውነት /Legal Personality / ያላቸውን የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅቶች፤

መ) የቀን ገቢ ሽያጭ ለመገመት የሚያስችግሩ በሥስተኛ ወገን ግብራቸው የሚወሰንባቸው የንግድ ዘርፎች (ህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ ላኪ፣ የነዳጅ ማደያ ወዘተ.)።

5. <u>የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም</u>

1/ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 አንቀጽ 3 እና በአንቀጽ 48 የግብር ከፋዮችን ደረጃ ለመወሰን እና የማናቸውንም ሰው የቀን ገቢ ለመገመትና ለመወሰን የሚከተሉት ኮሚቴዎች በዚህ መመሪያ ተቋቁመዋል፡-

ሀ) የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ፤

ለ) የወረዳ/የከተማ አስተዳደር የቀን ገቢ ግመታ ኢንስፔክሽን ኮሚቴ፣

ሐ) የወረዳ/ከተማ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮማቴ፣

መ) የዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ፣

ሠ) የክልል የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ፣

ረ) የ3ኛ ወገን የግብይት መረጃ አሰባሳቢ እና አቅራቢ ቡድን ይቋቋማል፣

2/ የግብር ከፋዮችን ብዛት እና የንግድ እንቅስቃሴውን ስፋት መሠረት በማድረግ የቀን ገቢ ገማች እና የቀን ገቢ ግመታ ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ብዛት ከአንድ በላይ ሊቋቋም ይችላል፤

3/ በወረዳ/በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች እያንዳንዳቸው ቢያንስ ከ4-5 አባላት ይኖራቸዋል፤

4/ የቀን ገቢ ለመገመትና ለመወሰን የቀን ገቢ ገማች እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ስብጥር እና የሥራ ድርሻ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል፡-

ሀ) የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ፣

1) ከገንዘብ ጽ/ቤት ተወካይ ወይም ከንግድ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ጽ/ቤት---------- ሰብሣቢ፤

2) የቀበሌ አስተዳደር ተወካይ (ከወረዳዎች/ከተሞች)---------- አባል፤

3) የነጋዴ ተወካይ ----------አባል፤

4) ከንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት----------አባል፤

5) የወረዳ/ የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ተወካይ ----------አባልና ፀሀፊ፤

ለ) የወረዳ/የከተማ አስተዳደር የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኢንስፔክሽን ኮሚቴ፤

1) የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ገንዘብ ጽ/ቤት ተወካይ ....ሰብሣቢ፤

2) የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ተወካይ.....አባል፤

3) የወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ተወካይ.....አባልና ፀሀፊ፤

5/ የመደበኛ ቁርጥ ግብር አፈጻጸሙን የሚከታተል፣ የሚገመግም እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴዎች አደረጃጀት እና ስብጥር እንደሚከተለው ተቋቁሟል፡-

ሀ) የወረዳው አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፡-

1) የወረዳው አስተዳዳሪ.....ሰብሳቢ፤

2) የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን ኃላፊ ..... አባል፤

3) የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ .....አባል፤

4) የንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል፤

5) የወረዳው ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል፤

6) የገንዘብ ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል፤

7) የፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ..... አባል፤

8) የንግድ ምክር ቤት ተወካይ..... አባል፤

9) የሰላምና ደህንነት ጽ/ቤት ኃላፊ..... አባል፤

10) የከተማና መሰረተ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ..... አባል፤

11) የገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባልና ፀሀፊ፤

ለ) የከተማ አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ፡-

1) የከተማው ከንቲባ..... ሰብሣቢ፤

2) የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል፤

3) የገንዘብ ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

4) የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

5) የንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

6) የፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

7) ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

8) የንግድ ምክር ቤት ተወካይ.....አባል፤

9) የሰላምና ደህንነት ኃላፊ.....አባል፤

10)የከተማና መሰረተ ልማት ኃላፊ.....አባል፤

11)የገቢዎች መምሪያ/ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባልና ፀሀፊ፤

ሐ) የዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፡-

1) የዞን አስተዳዳሪ .....ሰብሣቢ፤

2) የዞን ገንዘብ መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

3) የዞን ንግድና ገበያ ልማት መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

4) የፖሊስ መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

5) የዞን የመንግስት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

6) የዞን ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ.....አባል፤

7) የዞን ሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

8) የዞን ንግድ ምክር ቤት.....አባል፤

9) የዞን የሰላምና ደህንነት መምሪያ ኃላፊ.....አባል፤

10)የዞን የከተማና መሰረተ ልማት ኃላፊ .....አባል፤

11) የዞን የገቢዎች መምሪያ ኃላፊ .....አባልና ፀሀፊ።

መ) የክልል መስተዳድር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፡-

1) የክልል ር/መስተዳድር.....ሰብሣቢ፤

2) የገንዘብ ቢሮ ኃላፊ..... .....አባል፤

3) የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ..... አባል፤

4) የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ..... አባል፤

5) የፍትህ ቢሮ ኃላፊ.....አባል፤

6) የኮሚኒኬሽን ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ..... አባል፤

7) የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር..... አባል፤

8) የክልሉ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ኘሬዝዳንት..... አባል፤

9) የሰላምና ደህንነት ቢሮ ኃላፊ..... አባል፤

10) የከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ ..... አባል፤

11) የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ..... አባል፤

12) የገቢዎች ቢሮ ምክትል ኃላፊ .....አባልና ፀሀፊ።

6. ለቀን ገቢ ጥናት ሥራዎች የሚያስፈልጉ የኮሚቴ አባላት የሚመረጡበት የመመዘኛ መስፈርት

1/ በተለያየ ደረጃ ከተቋቋሙት የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ውጪ በሌሎች ኮሚቴዎች አባል ለሚሆኑ የመንግስት ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች አግባብነት ባለው መ/ቤት አቅራቢነት በአስተዳዳሪው ወይም በከንቲባው የሚመደቡ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሠረት የሚመደቡ ከመንግስት መ/ቤቶች እና ቀበሌዎች የሚወከሉ አባላት መምረጫ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) የሥነ-ምግባር ችግር የሌለባቸው

ለ) የከተማውን የንግድ እንቅስቃሴ እውቀት ያላቸው፤

ሐ) ስለ ግብር ዓላማ እና የመንግስት ገቢ በመሆኑ ለልማት ያለውን ፋይዳ በተሻለ የሚገነዘቡ፤

መ) የኮሚቴውን አሠራር በምስጢር መጠበቅ የሚችሉ፤

ሠ) በሥራ ትጋትና ተነሳሽነታቸው የሚታወቁ ፤ ኃላፊነት የመወጣት ብቃት ያላቸውና ከአድሏዊ አሠራር ነጻ የሆኑ፣

3/ ከንግዱ ማህበረሰብ የሚወከሉ የኮሚቴ አባላት በከተማው የንግድ ምክር ቤት አቅራቢነት የሚወከሉ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ምክር ቤት በሌለባቸው ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፣ ከነጋዴ ሴቶች ማህበር (ወዘተ...) ከንግዱ ማህበረሰብ የሚወከሉ የኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ከንግዱ ማህበረሰብ መወከል ካልተቻለ ወረዳዎች/ከተማ አስተዳደሮች በአስተዳደሪው/በከንቲባው ሰብሳቢነት ከንግዱ ኅብረተሰብ ተመርጠው ይወከላሉ፤

6/ ከንግዱ ማህበረሰብ የሚወከሉ የነጋዴ ተወካዩች መምረጫ መስፈርቶችም የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በንግድ ሥራ የካበተ ልምድ ያላቸው፤

ለ) በግብር ጉዳይ ተከሰው የማያውቁና የግብር ግዴታቸውን በአግባቡ የተወጡ ወይም ዕዳ የሌለባቸው፤

ሐ) በማህበረሰቡ መልካም ሥም ያላቸው እና

መ) በመንግስት ተቋማት ዕውቅና የተሠጣቸው፡፡

7. <u>በየደረጃው የተቋቋሙ ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልል ር/መስተዳድር ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የቀን ገቢ ግምት ጥናቱን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል ፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

ለ) ለጥናቱ የሚያስፈልገውን የቁሳቁስና ገንዘብ ይመድባል ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

ሐ) በየደረጃው መቋቋም የሚገባቸው ኮሚቴዎች ስለመቋቋማቸው ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

መ) ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ የጥናቱን ዓላማና ጠቀሜታ ተረድቶ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ድጋፍና ትብብር እንዲያደርግ የተጠናከረ ኮሚዩኒኬሽን ሥራ እንዲከናወን የአሠራር ሥርዓት መፈጠሩን ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

ሠ) ለዞን/ለከተማና ወረዳ አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ አባላት የተግባሩን አፈፃፀም አቅጣጫዎች ተገንዝበው የራሳቸውንም ማስፈፀሚያ ዕቅድ አቅደው እንዲንቀሳቀሱ የተሟላ ድጋፍ ይሰጣል፤

ረ) የተጠናው የቀን ገቢ ግምት ጥናት በየደረጃው ከተጠና በኋላም በግብር ከፋዮች፣ በንግድ ምክር ቤቶች፣ በዘርፍ ምክር ቤቶች፣ የነጋዴ ሴት ማህበር እንዲሁም ለሌሎች አጋርና ባለድርሻ አካላት አጠቃላይ በጥናቱ ዙሪያ እንዲተዋቸት ይደረጋል፣ አስተያዬቱና ትችቱም በግብዓትነት እንዲወስድ ያደርጋሉ፤

2/ የዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልሉ ግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዞኑ ዉስጥ የሚከናወኑውን የቀን ገቢ ግምት ጥናት አፈጻጸም በበላይነት ይከታተላል፣ ይመራል፣ የራሱን የማስፈፀሚያ ዕቅድ አጋጅቶ በማፀደቅ ይከታተላል፤

ለ) በየወረዳው ወይም በየከተማው መቋቋም የሚገባቸው ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ) እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ቀበሌ ድረስ ወርዶ የኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይገመግማል፣ ድጋፍና አመራር ይሰጣል፡፡

መ) ለክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ስለ አፈጻጸሙ በየሳምንቱ ሪፖርት ያስተላልፋል፣ ያገኘውን ግብረ መልስ የራሱን በመጨመር ወደ ታች ያወርዳል፡፡

ሠ) አቅጣጫ ከመሰጠት ባለፈ የቀን ገቢ ግምት በግብር ከፋይ ዝርዝር ደረጃ አንሷል ወይም በዝቷል በሚል የማስተካከል ሥራ ውስጥ አይገባም ነገር ግን የፍትሃዊነት ችግሮች ከወረዳ ወረዳ፣ ከከተማ ከተማ እንዲሁም በግብር ከፋይ ደረጃ ጥያቄዎች ሲያጋጥሙ እየገመገመ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

3/ የወረዳ/የከተማ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞን አስተዳደር እና ለዞኑ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) በወረዳው/በከተማው ውስጥ በየደረጃው መቋቋም ያለባቸው ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ የማስተባባር ሥራ ያከናውናል፣ ይቆጣጠራል፣ ይመራል ፤

ለ) ለወረዳው/ለከተማው አስተዳደር የቀን ገቢ ገማች እና የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች አስፈላጊ የሥራ ቁሳቁስ በወቅቱ መድረሱን ይከታተላል፣ ስለ የቀን ገቢ ግምት ጥናት ስልጠና እንዲያገኙ ያስተባብራል፣

ሐ) በጥናቱ ወቅት በየደረጃው ለሚያጋጥሙ ችግሮች እና ለሚነሱ ጥያቄዎች ከገቢ ጽ/ቤቶች ጋር በመሆን ምላሽ ይሰጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱ በሥራ ሂደት በሚያጋጥሙ የአሠራር ችግሮች ዙሪያ የማብራሪያ ጥያቄ ለዞንና ለክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣

4/ የወረዳው/የከተማው አስተዳደር የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው /ለከተማው የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለወረዳው/ከተማው ገቢዎች ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) የመረጃ ሰብሳቢ እና የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ሥራው በትክክል ስለመከናወኑ የክትትል ሥራ ይሰራል፤ ለአስተባባሪ ኮሚቴው እና ለጽ/ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል።

ለ) በሥራ ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች ወዲያውኑ ምላሽ እንዲያገኙ የሚያስችል የመፍትሄ ሃሣብ ለአስተባባሪ ኮሚቴውና ለገቢ ጽ/ቤቱ ያቀርባል።

ሐ) የቀን ግምት ጥናት መረጃ አሰባሰብ የሥራ ሂደቱን ከቀበሌ ቀበሌ ከግብር ከፋይ ግብር ከፋይ እና ጎናዊ እና አግድማዊ ፍትሐዊነቱን በጠበቀ መልኩ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ጥናት እየተከናወነ መሆኑን በማረጋገጥ መስተካከል አለባቸው የሚባሉ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ችግሮችን ለይቶ ተጠሪ ለሆነላቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤ የተሰጡ ማስተካከያዎች መተግበራቸውን ያረጋግጣል።

መ) የቀን ገቢ ግምት ጥናት የመጨመር ወይም የመቀነስ ተግባር ውስጥ አይገባም፤ ነገር ግን ጥናቱ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ ያገናዘበ መሆኑን ወይም ግብር ከፋዩን ገላጭ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ችግሮች እንዲታረሙ ያደርጋል፣ ተሞክሮ ያለዋወጣል።

ሠ) በየዕለቱ የተሰጡ የገቢ ገማች ኮሚቴዎችንና ጥናቱ ያካተታቸውን ግብር ከፋዮች ክትትል ያደርጋል፤

ረ) የሚያጋጥሙ ችግሮችን መስክ ድረስ ተገኝቶ ክትትል በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ለገቢ ጽ/ቤት ኃላፊው ያቀርባል፣

5/ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው/ለከተማው ገቢዎች ጽ/ቤት እና ለወረዳ/ለከተማ አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ) ሥልጣንና ተግባራት

1) በቀን ገቢ ግምት አቀራረብ ላይ ከማናቸውም ወገን ተጽእኖ ነጻ ሆኖ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መረጃ በግብር ከፋይነት የሚታወቁትንና ወደ ግብር መረቡ ያልገቡትን ለይቶ ይሰበስባል፣

2) የቀን ገቢ ግምት ለማቅረብ ማናቸውም መረጃ ከግብር ከፋዩ ለመጠየቅ ወይም ድርጅቱን ለመጐብኘት መብት እና ሥልጣን አለው፣

3) ተጨማሪ መረጃ ሲገኝ አጥኚ ኮሚቴው ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ የቀን ገቢ ግምት መረጃ የማስተካከል ሥልጣን ይኖረዋል፤

4) መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት እቃ የሚያሸሹ፣ የሚደብቁ እና ቤት ዘግተው የሚጠፉ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ የቀበሌ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ጥናቱን ለማካሄድ አስቸጋሪ ሆኖ ሲያገኝ ጥናቱን እንዲታለፍ ወይም እንዲቆይ ለገቢ ጽ/ቤቶች ያልተጠና መሆኑን በዝርዝር ያሳውቃል፡፡

5) የገቢ ጽ/ቤቱ ያልተጠኑ ድርጅቶችን በተለየ ሁኔታ እንዲጠኑ ኘላን ያወጣል፣ በዚሁ መሠረት ያስፈጽማል፣

6) በጥናት ወቅት ችግር የሚፈጥሩ ግብር ከፋዮች ካሉ መምከርና በምክር የማይታረሙትን እንዲጠየቁ ለጽ/ቤቱ ያሳውቃል፣

7) ከወረዳው/ከተማው አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት እና ከቀበሌ አስተዳደር የሚሰጠው የነጋዴ ዝርዝርና ኮሚቴው በራሱ ጥረት የሚያገኛቸውን በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችና ድርጅቶች የሥራ ቦታ በአካል በማየት እና በመገኘት በተዘጋጀው መጠይቅ መሠረት መረጃውን ይሰበስባል፡፡

8) በየእለቱ የሚሰበሰበውን የቀን ገቢ ግምት መረጃ በተዘጋጅው መጠይቅ ቅጽ ላይ በመፈራረም በየእለቱ ለወረዳው/ለከተማው ገቢ ጽ/ቤት ያቀርባል፣

9) ከወረዳው ዋና ከተማ ውጪ ያሉ ጣቢያ ከተሞች የሚቋቋሙ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴዎች በየእለቱ መረጃ ለመስጠት ስለሚያስቸግር በየሦስት ቀኑ ወይም የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴው በሚያስቀምጠው የጊዜ ሠሌዳ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ሰብሳቢ ለገቢዎች ጽ/ቤት መረጃ ይልካል ወይም በአካል ተገኝቶ ያስረክባል፣

10) በየዕለቱ አጭር የውሎ ግምገማ ያደርጋሉ የግምገማ ሪፖርቱን ከሌሎች ተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለወረዳው/ለከተማው ገቢዎች ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፣

11) በሣምንት የተሰሩትን ሥራዎች ከሌሎች ኮሚቴዎች ጋር የጋራ ግምገማ ያካሂዳሉ ስለ አፈጻጸሙ ሪፖርት ለገቢዎች ጽ/ቤት ያቀርባሉ ፣

12) የሥራ ቀናት በወረዳው/በከተማው አስተባባሪ ኮሚቴ የሚወሰን ሆኖ ቢያንስ በሳምንት 6 የሥራ ቀናት መሰራት ይጠበቅባቸዋል፣ እንደሁኔታው ሙሉ ሳምንቱን በመስራት ተግባሩን በፍጥነት ማጠናቀቅ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

13) ከቀበሌው አስተዳደር ለኮሚቴው አገልግሎት የሚውል ጊዜያዊ ቢሮ በፀሐፊው አማካይነት መረከብ ይኖርባቸዋል፣

14) ለገቢ ግምቱ ሥራ ማስፈጸሚያ ከገቢ ጽ/ቤቶች የሚላኩ ቅጾችን፣ መመሪያዎችን የነጋዴዎችን ዝርዝር መዛግብት ወዘተ በፀሐፊው አማካይነት ይረከባሉ፣

15) ከገቢዎች ጽ/ቤት የግብር ከፋዮችን ዝርዝር መረጃ መረከብና ከንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት የነጋዴዎችን ዝርዝር ለማነፃፀሪያነት መያዝ ይኖርባቸዋል፣

16) በቀበሌው ውስጥ ያሉትን የግብር ከፋዮች የሥራ ቦታ በመለየት የጉብኝት የሥራ መርሃ ግብር ማውጣት፣

17) በወጣው መርሃ ግብር መሠረት በንግድ ድርጅቶች እየተገኘ በተሰጠዉ ዝርዝር መረጃ መሰረት ጉብኝት የማድረግ፣

18) መረጃዎችን በተዘጋጀው ቅጽ መሙላትና ለጥያቄው ምላሽ የሰጠውን ግብር ከፋይ ማስፈረም፣

19) ለሥራው በተሰጠው የጊዜ ሠሌዳ የንግድ ድርጅቱ ክፍት ሆኖ ካልተገኘ አካባቢ መጠየቅና ኮሚቴው ከአካባቢውና ከሚያውቃቸው መረጃዎች ወይም እውነታዎች በመነሳት የቀን ገቢ ግምት ይገምታል። ይሁን እንጅ ኮሚቴው ለመገመት የማይችል ሆኖ ሲገኝ በገቢ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጥናቱ በሌላ ጊዜ የሚጠና ወይም የሚከናወን_ይሆናል።

20) በእይታው፣ በግብር ከፋዩ ከተሰጠው የግብይት መረጃ እና ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገኘው የግብይት መረጃ በመነሳት የቀን ገቢ ግምት በድምጽ ብልጫ መወሰን፣

21) የእለቱ የተጐበኙ የንግድ ድርጅቶችን ዝርዝር በተዘጋጀው መመዝገቢያ ቅጽ በፀሐፊው አማካኝነት ማስፈር፣

22) ሥራው ሲጠናቀቅ ጥራዙ ላይ የቀረበውን በንምራ ቁጥር ቅደም ተከተል በመዘርዘር የተበላሹም ካሉ የተበላሹ ስለመሆናቸው በመግለጽ በመረካከቢያ ቅጽ ሞልቶ ለወረዳው/ከተማው አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ማስረከብና የርክክብ ቬርቫሉን ቅጅ መያዝ አለበት።

23) መረጃዎች በወረቀትና በስስ ቅጅ ተዘጋጅተው (ስካን) ተደርገው ወይም በፒዲኤፍ መልክ ታስሮ ለገቢ ጽ/ቤቶች ማስረከብ፣

ለ) የኮሚቴው ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1) ከቀበሌው አስተዳድር ለኮሚቴው ጊዜያዊ ቢሮ ይረከባል፣

2) ለጥናቱ ሥራ ማስፈጸሚያ ከገቢዎች ባለስልጣን የተላኩ ቅጾችን፣ መመሪያዎችን፣ ይረከባል የነጋዴ ዝርዝር ከወረዳው/ከተማው አስተዳደር ንግድና ገበያ ልማት ጽ/ቤት ይረከባል፣

3) የተረከባቸውን ሰነዶች በአግባቡ በሥራ ላይ ያውላል፣ እንዲሁም ሰነዶች ተገቢውን ጥንቃቄና ጥበቃ ያደርጋል፣

4) በየእለቱ የተጐበኙ የንግድ ድርጅቶችን ዝርዝር ለዚሁ በተዘጋጀው መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ይመዘግባል፣

5) እያንዳንዱ የቀን ገቢ ግምት ጥናት የመገመቻ ጥራዝ ሲጠናቀቅ በንምራ ቁጥር ቅደም ተከተል በተዘጋጀው መመዝገቢያ ላይ ይመዘግባል፣

6) በሥራ ላይ ያልዋሉትንና የተበላሹ የመገመቻ ቅጾች ካሉ ንምራ ቁጥራቸው ተገልጾ በመረካከቢያ ቅጽ ላይ ተሞልቶ ለወረዳው/ከተማው አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ በማስረከብ የርክክቡን ቀሪ ይይዛል፤

7) ከአስተዳደርና ፀጥታ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ፣ ከፖሊስ፣ ከፍትህ፣ ከቴክኒክና ሙያ ወዘተ. ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰበስባል።

8. <u>ክልልና በተዋረድ ያሉ የገቢ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ተጠሪነቱ ለክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ) የጥናቱን አፈጻጸም ዝርዝር የሥራ መርሃ ግብር፣ የሚያስፈልግ በጀት በማዘጋጀት ለክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል።

ለ) የቀን ገቢ ግምት ጥናትን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት የቴክኒክ ስልጠና እና የአካል ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፣

ሐ) መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉ የሥራ ማንዋሎች፣ መጠይቆች፣ ቅጾችን ያዘጋጀል ያሰራጫል፣

መ) ጥናቱን በዞን፣ በከተማ እና በወረዳ ለሚመሩና ለሚያከናውኑ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣

ሠ) ከክልል የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አመራር መሠረት የሰው ኃይል ስምሪቱን ይከታተላል፣

ረ) የቀን ገቢ ግምት ጥናት በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ከዞን ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ጋር በመቀናጀት በወረዳ/በከተማ በመገኘት ናሙና በመውሰድ የመረጃ አሰባሰቡን ሂደት ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ግድፈቶች ካሉም በአስቸኳይ እንዲታረሙ ያደርጋል፣

ሰ) ከወረዳዎች እና ከከተሞች በዞን ደረጃ ተጠቃሎ የሚመጣለትን የግብር ከፋዮች መረጃ በማጠናቀርና በመገምገም ለክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ሸ) የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ጥናቱ እንዲፈፀም አቅጣጫ ይሰጣል፣ ተሞክሮ ቀምሮ ያስተላልፋል፤

2/ የዞን ገቢዎች መምሪያ ተጠሪነቱ ለክልሉ ገቢዎች ቢሮ እና ለዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፤

ሀ) ጥናቱን በባለቤትነት የሚመራ በመሆኑ የክልሉን መነሻ በማድረግ ዝርዝር መርሃ-ግብር በማዘጋጀት የራሱን የሥራ መርሃ ግብር ያዘጋጀል ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡

ለ) በየደረጃው ለሚቋቋሙና ወደ ሥራ ለሚሠማሩ የመደበኛ ቁርጥ ግብር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለቀን ገቢ ገማች ኮሚቴዎች ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣

ሐ) ለቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ለጥናት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በሙሉ መቅረባቸውን ይከታተላል፡፡

መ) በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች ከክልሉ ገቢዎች ቢሮ እና ከዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመመካከር መፍትሄ ይሰጣል፣

ሠ) በወረዳው/በከተማው የሚከሰቱ የአሠራር ግድፈቶችን ከግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እና ከወረዳ/ከተማ ከገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በመወያየት መፍትሄ ይሰጣል፣

ረ) የቀን ገቢ ግምት ጥናት ሪፖርት በየሳምንቱ ለክልሉ ገቢዎች ቢሮ ያስተላልፋል፣

ሰ) ከተሞችና ወረዳዎችን የተጠናከረ ችግር ፈቺ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ ተሞክሮ እየቀመረ ያለዋውጣል፤

3/ የባህር ዳር ከተማ፣ ጐንደር፣ ደሴ፣ ደ/ብርሃን፣ ደ/ማርቆስ፣ ኮምቦልቻ፣ ወልዲያ እና ደ/ታቦር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች መምሪያ ጽ/ቤት ተጠሪነት ለከተማው አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴና ለክልሉ ገቢዎች ቢሮ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የከተማ/የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ተጠሪነታቸው ለወረዳው/ለከተማው አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ

አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለዞን ገቢዎች መምሪያ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

ሀ) በወረዳው/በከተማው ውስጥ የሚከናወን የቀን ገቢ ግምት ጥናት በባለቤትነት ከወረዳው/ ከከተማው አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ ጋር በመሆን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፡፡

ለ) የራሳቸውን የተግባር ማስፈፀሚያ ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፣

ሐ) ከወረዳው/ከከተማው አስተዳዳሪ/ከንቲባ ጋር በመመካከር በየደረጃው መቋቋም ሚገባቸው የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡

መ) በኮሚቴ አባልነት የሚወከሉ ባለሙያዎች በወጣው መስፈርት ወይም መመዘኛ መሠረት ስለመሆኑ ያረጋግጣል፣ለሚሰማሩ አካላት እንደ አስፈላጊነቱ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

ሠ) በጥናት ሥራው በሚሠማሩ የኮሚቴ አባላት ማንነታቸውን የሚገልጽ የደረት መታወቂያ (ባጅ) እና ደብዳቤ ይዘጋጃል፣ የጥናቱ ትክክለኛ እና ታማኝነት መኖሩን ያረጋግጣል፤

ረ) ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶችንና አስፈላጊ የሚላቸውን የግብር ከፋይ መረጃዎችን ለቀን ገቢ ገማች እና ለቀን ገቢ ግምት ጥናት ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ያቀርባሉ

ሰ) የቀረበው የቀን ገቢ ግምት መረጃ ትክክል አይደለም ብሎ ሲያምንበት እንደገና እንዲታይ ከነምክንያቱ ለቀበሌ መረጃ ሰብሳቢና የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ ሊመልስ ይችላል፣

ሸ) የቀበሌው የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ የሚያቀርበውን የቀን ገቢ ግምት ትክክል መሆኑን አረጋግጦ የገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ ያፀድቃል፣

ቀ) ግብር ከፋዮች ከሥስተኛ ወገን የሚሰበሰብ የግብይት መረጃ ያላቸው ከሆኑ በአካባቢ ሽያጭ ከሚያከናውኑት የዕለት ገቢ ጋር ተዳምሮ ወይም ተጨምሮ መረጃው ይሰበሰባል፣ በዚሁ መሠረት በአካባቢው ግብር ከፋዩ የሚያከናውነው ሽያጭ መጠንና ከሥስተኛ ወገን የሚመጣ ወይም የተገኘ መረጃ ግምት ውስጥ ገብቶ የግብር ከፋዩ ዓመታዊውን መረጃ የሚጠናቀር ይሆናል፡፡

በ) በአጠቃላይ የቀን ገቢ ግምት ጥናትን በተመለከተ ለዞን ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት፣ ለወረዳው/ለከተማው የገቢ ግምት አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡ ለሚቀርቡ

ጥያቄዎች ተገቢ ማብራሪያ ይሰጣል የቴክኒክ ሥራውን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል። በአሠራር ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች ለአስተባባሪ ኮሚቴው በማቅረብ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል።

ተ) የቀን ገቢ ግምት ጥናት ከማስፀደቁ በፊት ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚገልጽ ስለመሆኑ በንግድ ምክር ቤቶች በዘርፍ ማህበራትና በነጋዴ ሴቶች ማህበር የማስተቸት ሥራ ያከናውናል፣ በየደረጃው የህዝቡን ባለቤትነት ያረጋገጠ እንዲሆን ያደርጋል፤

9. <u>የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት</u>

1/ የሥራ ሰዓት ስለመወሰን

ሀ) የቀበሌ መረጃ ሰብሳቢና የቀን ገቢ ግምት ገማች ኮሚቴዎች የሥራ ሰዓት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ጠዋት ከ2:30 — 6:30 እና ከሰዓት ከ7:30 — 11:30 ይሆናል። እሁድን በተመለከተ በአስተባባሪ ኮሚቴው የሚወሰን ይሆናል።

ለ) ለሥራ ምቹ ያልሆኑ አካባቢዎች የሥራ ሰዓቱን በሚመለከት አስተባባሪ ኮሚቴው በሚወስነው መሠረት ይሆናል፤

ሐ) ምሽት ቤቶች ባሉባቸው ከተሞች ጥናቱ ከፀጥታ አካላት ጋር በትብብር ማታ ላይ እንዲጠና ይደረጋል፣

2/ ውሳኔ አሰጣጥና ምልዐተ - ጉባዔ ስለመወሰን

ሀ) መረጃ በመሰብሰብና ውሣኔ በመስጠት ሂደቶች ሁሉም የኮሚቴ አባላት በሙሉ የመገኘት ግዴታ አለባቸው።

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የኮሚቴ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከሁለት ቀናት በላይ ከቀረ እና ጭራሽ መገኘት የማይችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በሌላ የኮሚቴ አባል ተክቶ ማሠራት ወይም ተክቶ ማቆየት ያስፈልጋል።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) መሠረት የሚተካው የኮሚቴ አባል መምጣት ከነበረበት የሥራ ክፍል ማለትም ከንግዱ ከሆነ ከንግዱ ህብረተሰብ፣ የመንግስት ሠራተኛ ከሆነ ከመንግስት መ/ቤት ይሆናል ማለት ነው።

መ) ከመረጃ ሰብሳቢዎች/የቀን ገቢ ግምት አጥኚዎች ሁለት ሦስተኛ (2/3 ኛው) ከተገኙ ሥራውን ማከናወን ይችላሉ። ስብሰባውንም በዚሁ መሠረት ያካሂዳሉ።

ሠ) ማናቸውም የቀን ገቢ ግምት ጥናት ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ የሚወሰኑ ይሆናል። ድምጹም እኩል ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል። ውሳኔውም የኮሚቴው ውሣኔ ሆኖ ተወስዶ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

3/ የአሠራር ስልቶች

ሀ) ሥራውን ለመጀመር የሚያስችል የቅድሚያ ቅኝት መነሻ የሚሆን የነጋዴዎችን ዝርዝር መረጃ ከገቢ ተቋሙ ይረከባል፣

ለ) የሚወጣውን አመቺ መርሃ ግብር ተከትሎ ለጉብኝት የሚያስችል ከራሳቸው ዝርዝር መረጃ ጋር አገናዝበው ያደራጃሉ፤

ሐ) ለግብር ከፋዮች በተዘጋጀው የዕለት ገቢ ግምት መረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ መሠረት ግብር ከፋዮችን የቀን ገቢ ግምት በመጠየቅ ግብር ከፋዮች የሚሰጡትን ምላሽ በመጠይቁ መሠረት በሙላትና የሰጡት መረጃ ትክክል ስለመሆኑ ግብር ከፋዮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣

መ) በአሞላል ላይ ስህተት ካጋጠመ ቅጹ ተሰርዞና ታጥፎ ከጥራዙ ውስጥ (Void) መደረጉ ተገልጸና ከሌላ መገመቻ ቅጽ ጋር ተወራርሶ መቀመጥ ይኖርበታል፣ የተሠረዘ ወይም የተደለዘ ጥራዝ ወይም ቅጽ አገልግሎት ላይ አይውልም። ይህንን የተጠቀመ አካል ተጠያቂ ይሆናል።

ሠ) ከንግዱ ህ/ሰብ የተወከሉ የኮሚቴ አባላት የራሳቸው የንግድ እንቅስቃሴ የቀን የገቢ ግምት ጥናት ሲካሄድ በቀን ገቢ ግመታ ሥራ ላይ የሚሳተፉ አይሆንም፣

ረ) በመጠይቁ ያልተገለጹ/ያልተመለከቱ ለገቢ ግምቱ አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎች ሊያጋጥሙ በቅጹ ልዩ መግለጫ ማስታወሻ ላይ ተመዝግበው እንዲያዙ ይደረጋል፣

ሰ) ግብር ከፋዩ ሽያጭና ግዥውን በተመለከተ የሚይዛቸው መዛግብት ወይም ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ በመጠየቅ ማስታወሻዎች ይያዛል፣

ሸ) ከዕለቱ ቅኝት በኋላ በተመደበው ጽ/ቤት በመሰብሰብ የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን የቀን ገቢ ግምት ውሣኔ መካሄድ ይኖርበታል፣

ቀ) በመጨረሻ የተደረሰበት የቀን ገቢ ግምት ውሣኔ በአባላቱ ፊርማ መጽደቅ አለበት፣

በ) የቀበሌ ገቢ ገማች ኮሚቴ ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ሥራዎች በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሚከናወን ይሆናል።

4/ ቃለ - ጉባኤ ስለመያዝና ሚስጢር ስለመጠበቅ

ሀ) ማንኛውም ኮሚቴ ተወያይቶ ውሣኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች በቃለ -ጉባኤ መመዝገብ አለባቸው።

ለ) ኮሚቴው ተልዕኮውን አጠናቆ ሲጨርስ ማናቸውንም የሥራ ሰነዶችና የቃለ ጉባኤ መዝገቦች በየደረጃው ለተቋቋመበት ወረዳ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ያስረክባል።

ሐ) የኮሚቴ አባላት የኮሚቴውን አሠራር ምስጢር መጠበቅ ይኖርበታል።

10. <u>የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴዎች ተጠያቂነት</u>

ማናቸውም የኮሚቴ አባል የቀን ገቢ ግምት መረጃ አሰባሰብ እና የቀን ገቢ ግምት አወሳሰን የሥራ ሂደቱን የሚያሰናክልና የሚጐዳ ወይም የኮሚቴ ምስጢር ያባከነ እንዲሁም ሆን ብሎ ግብር ከፋዩን የሚጠቅም ወይም የሚጐዳ ሥራ የፈጸመ መሆኑ ሲረጋገጥ ከኮሚቴ አባልነት ተሰርዞ አግባብ ባለው የግብርአስተዳደር ሕግና በሌሎች የወንጀልና የፍታብሔር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፣

11. <u>የኮሚቴ አባላት አበል አከፋፈልን በተመለከተ</u>

1/ በኮሚቴ ሥራ የተሰማሩ የቀን ገቢ ጥናት ሥራ በሚያከናውኑ የቀበሌ የቀን ገቢ ግምት ጥናት መረጃ ሰብሳቢ፣ የቀን ገቢ ግምት ጥናት አጥኝ እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ የቡድን አባላት የውሎ አበል አከፋፈልን በተመለከተ በሚከተለው አኳኋን እንዲከፈላቸው ይደረጋል።

ሀ) የምሳ አበል በቀን ብር 200.00/ሁለት መቶ ብር/ ይከፈላቸዋል። ከሥራ ባህሪው አንፃር ማታ በሚያጠኑበት ጊዜ ብር 300(ሦስት መቶ ብር) ይከፈላል።

ለ) የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ አባላት በአማካይ በቀን ከ20 እስከ 30 በሳምንት ደግሞ ከ120 እስከ 180 ግብር ከፋዮችን ማጥናት ይጠበቅባቸዋል፤

12. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

1/ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 7 መሠረት በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የአመራር አካላት ለግብር አስገቢው ባለስልጣን የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

ሀ) ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የግብር ከፋዩ መረጃዎችን ለግብር አስገቢው ወይም ለአጥኚ ኮሚቴዎች ሲጠየቁ በመስጠት፣

ለ) ለጥናት ኮሚቴ ሰብሳቢነት፣ አባልነት እንዲሠሩ የሚመረጡ አባላትን መርጦ የመላክና ተግባራቸውን በሚገባ እንዲፈጽሙ የመከታተል ግዴታ አለባቸው፣

ሐ) የቀን ገቢ ግምት ጥናት ሊያሰናክሉ የሚችሉ ቅስቀሳዎችን መከታተል፣ መቆጣጠር እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

13. ስለክትትል፣ ድጋፍ እና ሪፖርት አቀራረብ

1/ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴ/የቀን ገቢ ግምት ጥናት

ሀ) የቀበሌ የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኮሚቴ ለወረዳ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት እና ለወረዳ/ከተማው የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

ለ) በየቀኑ የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየት ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤትና ለአስተባባሪ ኮሚቴው ያቀርባሉ፣

ሐ) ለገቢ ጽ/ቤት በየቀኑ ሥራውን በተመለከተ የውሎ ግምገማ ውጤትና የቀን ገቢ ግምት ጥናት መረጃ ያቀርባሉ፣

መ) በንግዱ ማህበረሰብ የሚታዩ ክስተቶችን በሪፖርት ለገቢዎችና ለአስተባባሪ ኮሚቴው ያቀርባሉ፣

2/ የቀን ገቢ ግምት ጥናት ኢንስፔክሽን ኮሚቴ

1. ለወረዳው/ለከተማው ገቢዎች ጽ/ቤትና ለአስተባባሪው ኮሚቴ ሥራውን በሚመለከት ሪፖርት በየ2 ቀኑ ያቀርባሉ።

2. የሪፖርቱ ይዘት የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) በአሠራር ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት እና የመፍትሄ ሀሣቦችን ያካተተ ሪፖርት ያቀርባል

ለ) የቀበሌ የቀን ገቢ ገማች ኮሚቴው ሥራውን በትክክል እየተወጣ ስለመሆኑና በየቀበሌው ያሉ ጠንካራ ተሞክሮዎችና መታረም ያለባቸው ግድፈቶችን በመለየት እንዲስተካከሉ ሀሣብ ያቀርባል።

ሐ) ከቀበሌ መረጃ ሰብሳቢ ኮሚቴዎች ላይ የሚስተዋሉ የአሠራር ችግሮችንና በቀን ገቢ ግምት አጠናን ስልቶች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሀሣብ ማቅረብ፤የግብር ከፋዮችን መረጃ ጥናቱን አፈጻጸም በጥብቅ ይከታተላል፤

መ) በየቀበሌው በመዘዋወር የተጠኑ እና ያልተጠኑ ቤቶችን ክትትል ያደርጋል ለጥናት ኮሚቴው ግብዓት ይሠጣል።

3/ ገቢዎች ጽ/ቤት

የወረዳው /የከተማው ገቢዎች ጽ/ቤት ለዞን ገቢዎችና ለወረዳው/ለከተማው የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ በየሳምንቱ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያሳይ የተሟላ ሪፖርት ያቀርባል። በየቀኑ በስልክ ተፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል።

4/ የወረዳ/የከተማ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ

ለዞን የግብር ሥርዓት ማሻሻያ ኮሚቴ በየሳምንቱ የተሟላ ሪፖርት ያቀርባል።ይሁን እንጅ ወቅታዊና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን በየቀኑ መረጃዎችን በስልክ ያስተላልፋል።

5/ ዞን ገቢዎች መምሪያ፣

ለክልሉ ገቢዎች እና ለዞን የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ በየሳምንቱ የተሟላ ሪፖርት ያቀርባል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በየእለቱ በስልክ ስለ ጥናት ሥራው እንቅስቃሴ መረጃዎችን ይሰጣል።

6/ የዞን አስተዳደር የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ፣

ሀ) በየሳምንቱ ለክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል። እንደ አስፈላጊነቱ በየእለቱ በስልክ ስለ ሥራው እንቅስቃሴ መረጃ ይሰጣል፣

ለ) ከየወረዳው/ከየከተማው በሚደረገው ሪፖርት መሠረት ተሞክሮ እንዲወሰድ የተሻለ አሠራር እንዲፈጠር ተሞክሮዎችን ከወረዳ ወረዳና ከከተማ ከተማ ያለዋውጣል።

7/ የክልል ገቢዎች ቢሮ፣

ሀ) ለክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ በየሣምንቱ የተሟላ ሪፖርት አጠናቅሮ ያቀርባል። አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እና ያጋጠሙ ችግሮችን ... ወዘተ በየእለቱ በስልክ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል።

ለ) የተሻሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች ዞኖችና ከተማ አስተደደሮች ያስተላልፋል

ሐ) በመስክ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል

8/ የክልሉ የግብር ሥርዓት ማሻሻያ አስተባባሪ ኮሚቴ፣

ሀ) የሚላክለትን ሪፖርት በየሣምንቱ ይገመግማል፣

ለ) የመስክ ክትትል ያደርጋል፣

ሐ) የአሠራር ግድፈቶች ካሉ የማስተካከያ አቅጣጫ ይሰጣል፣

መ) አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ የአሠራር መመሪያ ያስተላልፋል።

14. <u>የግብር ከፋዮች ግዴታ እና ተጠያቂነት፣</u>

1/ ግብር ከፋዮች የራሳቸውን መረጃ ለመረጃ ሰብሳቢ ኮሚቴው የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

2/ ግብር ከፋዮች ንብረት በማሸሽ፣ እቃ በመደበቅ፣ ቤት በመዝጋት እንዲሁም ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ተባባሪ በሳይሆኑ ከተገኙ በገቢ ግበር አዋጅ 240/2008 እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

3/ መረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ግብር ከፋይ በወቅቱ መረጃ ባለመስጠት ወይም የኮሚቴውን ተግባር የሚያደናቅፍ፣ የተሳሳተ መረጃ ሆን ብሎ በመስጠት ለሚፈጠረው ችግር ኃላፊነቱን ግብር ከፋዩ የሚወስድ ይሆናል።

15. <u>ተግባሩ ተጀምሮ የሚጠናቀቅበት ጊዜ</u>

ከ---------- እስከ----------ቀን /2015 ዓ.ም ሥራው ይጠናቀቃል።

16. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

1/ ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ግንቦት---- ቀን 2015 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በገንዘብ ቢሮ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

መሠረት አዱኛ

የገንዘብ ቢሮ ም/ ኃላፊ